# በውይይቱ ይሳተፉ.

የተማሪዎች ድልድል እና የዲ.ሲ. የሕዝብ ትምህርት ቤት ወሰኖች ግምገማ ሂደትን የተመለከተ
የማህበረሰብ ስብሰባዎች





# የተማሪዎች ድልድል ፖሊስ ንድፈ ሀሳብ ሪቂቅ

አዘጋጅ፣ በተማሪዎች ድልድል የተማሪዎች አማካሪ ኮሚቴ









ሰኔ 11 ቀን 2014 ዓ.ም.

# ደብዳቤ ከአማካሪ ኮሚቴ

## ውድ የሕዝብ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች እና ሌሎች የማህበረሰብ ዓባላት፣

ከተማችን የተማሪዎች ድልድል ፖሊሲዎችን፣ የትምህርት ቤት ወሰኖችን እና የዝውውር ሂደትን በማሻሻል ብዙ የሚቀረው አለ። ዲስትሪክቱ ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ እነኝህን ጉዳዮች በተመለከተ አጠቃላይ ግምገማ አላደረገም። በእነዚህ አስርት ዓመታት ውስጥ ከተማችን ሰፋ ያለ የሕዝብ፣ የትምህርት፣ የኢኮኖሚ እና የዴሞግራፊ ለውጦች አይቷል። በደርዘን የሚቆጠሩ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ተዘግተዋል፣ ሌሎች ተከፍተዋል፣ አቅጣጫቸውን ለውጠዋል ወይም የፕሮግራማቸውን ትኩረት ወይም የክፍል ደረጃቸውን ለውጠዋል። የዲስትሪክቱ ቻርተር ትምህርት ቤት ክፍል - በ1996 ዓ.ም. የተመሠረተው - አሁን 44 ከመቶ የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና 58 የተለያዩ የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎችን ያጠቃልላል። ከተማችን ለውጥ ማድረግ እየቀጠለች ነው፣ በትምህርት ቤት ዕድሜ ያለው የሕዝባችን ቁጥር ከአሁን አንስቶ እስከ 2022 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ 50 ከመቶ እንደሚጨምር ይገመታል። ይህ ለከተማችን የሚያስደስት ጊዜ ሲሆን፣ ሁሉንም የዲስትሪክቱን ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸውን ለማገልገል የትምህርት ቤት ሥርዓታችን በነዚህ ለውጦች ላይ ማሰብ እና ምላሽ መስጠት አለበት።

በጥቅምት 2013 ዓ.ም. የትምህርት ምክትል ከንቲባ አቢጌል ስሚዝ መረጃዎችን የሚመረምር፣ ችግሮችን የሚጠቁም እና የመፍትሄ ሀሳቦችን የሚያቀርብ የተማሪዎች ድልድል አማካሪ ኮሚቴ ሾሙ። የኮሚቴው ዓባል እንደመሆናችን፣ ግልጽነትን፣ ጉልህነትን ለማሻሻል እና ለቤተሰቦች ተስማሚ የሆነ ጥራት ያለው የትምህርት ቤት አማራጮችን በእኩልነት የማግኘት ፖሊሲ እና የዕቅድ አስተያየቶች ለከንቲባው እንድናቀርብ ተጠይቀናል።

ከሂደቱ አጀማመር እና ለወራቶች ባካሄድነው ሥራ አዲስ የተወጠኑ ምርምሮችን እና ሰፊ መረጃዎችን ገምግመናል። በህዳር ወር 2013 ዓ.ም. በከተማው ባሉ በእያንዳንዱ ዋርዶች የትኩረት ቡድን ስብሰባዎች በማካሄድ የህዝብ አስተዋጾ ተጀመረ። ወደ 200 የሚሆኑ ወላጆች በተማሪዎች ድልድል እና የትምህርት ቤት ምርጫን በተመለከተ የመጀመሪያ አስተዋጽዖ አደረጉ፣ እንዲሁም ፖሊሲን እና የወሰን ለውጦችን በሚመራው ደንብ ላይ ሀሳብ ሰጡ።

ከትኩረት ቡድን ስብሰባዎች በኋላ ኮሜቴው ሶስት የፖሊሲ ምሳሌዎች አቅርቦ፣ በሚያዝያ ወር 2014 ዓ.ም. የትምህርት ምክትል ከንቲባው በተከታታይ የሥራ ቡድኖች ስብሰባ ለህዝብ ሀሳብ እንዲሰጥበት አቅርበውታል። ከ800 በላይ የሚሆኑ ኗሪዎች በሥራ ቡድን ስብሰባዎቹ ላይ ተሳተፈዋል። በተጨማሪም፣ ባለፉት ስምንት ሳምንታቶች፣ የትምህርት ምክትል ከንቲባው እና ብዙዎቻችን በርካታ የአካባቢ እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስብሰባዎች ከመቶ በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት በመላ ከተማው ተካፍለናል። እንዲሁም በመቶ የሚቆጠሩ የኢሜይል ጥያቄዎች እና ሀሳቦች ተቀብለን መልስ ሰጥተናል።

ሂደቱ በሙሉ ትኩረት የሰጠው በትምህርት ቤት መሻሻል ላይ ሳይሆን በተማሪ ድልድል በመሆኑ የማህበረሰብ ዓባላት ብሶታቸውን ገልጸዋል። ብሶታቸው ይገባናል፣ ስለዚህም አስተያየታችንን መሠረት የምናደርገው ከተማ አቀፍ የሆነ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ እና በማንኛውም በከተማው ውስጥ እርግጠኛ እና አድሎ የሌለው ከፍተኛ ጥራት ያለው የአካባቢ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሥርዓት እንዲኖር ቁጥራቸው በዛ ያለ ወላጆች እና ኗሪዎች በሰጡት አስተያየት መሠረት ነው። ቤተሰቦች የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን የሚያገኙበትን ዘዴ ማሻሻል እና የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን የመማሪያ ዞኖችን እና የዝውወር መንገዶችን ግልጽ ማድረግ ከቤተሰቦች፣ ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቦች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያረጋጋ እና የሚያጠናክር እንዲሁም ለትምህርት ቤቶች መሻሻል አስተዋጾ የሚያደርግ እንደሚሆን እናምናለን።

በመረጃ ላይ ያተኮረው ውይይት ጠቃሚ እና ሞቅ ያለ የተጠቃሚዎች ክርክር ይህንን የከተማ አቀፍ የአካባቢ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሥርዓት ራዕይ ለማካሄድ ዲስትሪክቱ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፣

- ግልጽነትን፣ ቅንብርን እና በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና ቻርተር ትምህርት ቤቶች በአንድነት እቅድ ማውጣት እና የለሁሉቱንም ኃላፊነት ማሻሻል።
- የሕዝብ ቁጥር መጨምርን እና የመጓጓዣ ችግሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንድ የተዘጉ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን እንደገና መክፈት።
- በመላው የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች አካባቢ በተለይ ከፍተኛ ችግሮች ያለባቸው ልጆችን ለሚያገለግሉት የገንዘብ
- ጭማሪ ማድረግ።
- ለተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ወደ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የመመላለሻ ችግሮችን መፍትሄ መስጠት።
- ተማሪዎች በብዛት በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች መካከል በሚዘዋወሩበት ጊዜ የሚፈጠረውን ውዝግብ መቀነስ።

ይህ የመጀመሪያ አስተያየት በርካታ በሆኑ መረጃዎች እና በህዝብ አስተዋጾ መሠረት መፍትሄ ለማግኘት ያደረግነውን ጥረት ያንጸባርቃል። ይህን ረቂቅ አስተያየት ይፋ ስናደርግ ፍጹም እንዳልሆነ እያወቅን ነው። በተለይም፣ በተሰጠው የወሰን ለውጦች እና የዝውውር መንገዶች የሕዝቡን ተጨማሪ አስተያየት ማግኘት እንፈልጋለን። በተጨማሪም ከተማ አቀፍ የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ሥርዓት እንዲኖሩ ስንገፋፋ፣ በትምህርት ቤቶቻችን ያሉትን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እና የተለያዩ ዘሮች እንዲጠናከሩ እና የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ዘዴዎችን ስንቀርፍ እና ሁሉም ትምህርት ቤቶች በአደጋ ጫፍ ላይ ያሉ ተማሪዎችን ለማስተማር ኃላፊነት እንዲወስዱ ስንገፋፋ ውጤታማ ለማድረግ አስተያየቶችን ለማግኘት ተስፋ እናደርጋለን። ለከንቲባው የመጨረሻውን አስተያየት ከመስጠታችን በፊት ይህንን ረቂቅ እንድናሻሽል አስተያየታችሁን እና አቋማችሁን እንድታካፍሉን እንጋብዛችኋለን።

በአንድነት ለመሥራት እንቀጥል።

ከምስጋና ጋር፣

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የተማሪዎች ድልድል አማካሪ ኮሚቴ

# የዚህ አስተያየት መሠረታዊ መዋቅር

የአማካሪ ኮሚቴው አስተያየቱን መሠረት ያደረገው በሚከተሉት ደንቦች ላይ ነው፣

- ለቤተሰቦች ጉልህ የሆነ የሕዝብ ትምህርት ቤት ዝውውሮች።
- በእያንዳንዱ አካባቢ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የሙብት ትምህርት ቤቶች።
- ከምድብ ትምህርት ቤቶች ምርጫ ውጭ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምርጫ ማግኘት።
- በአቅራቢያ የሚገኝ እና ያለስጋት የሚደረስባቸው የዲስ የህዝብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።
- ሁሉን ያካተተ የተማሪዎች ምዝገባ።
- የተሳካ እና ቀልጣፋ ከተማ አቀፍ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተቋም።

ከላይ ከተጠቀሱት ደንቦች ጋር ለማጣጣም፣ አማካሪ ኮሚቴው ከአንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዝውውር መሠረታዊ የሆነ በክልል የተመሠረቱ ትምህርት ቤቶች እና በጂኦግራፊ የተወሰኑ የዝውውር ሂደቶች ሀሳብ ያቀርባል። በአካባቢ ብቻ የተወሰነ ጥብቅ የሆነ የድልድል ሥርዓት የሚያስከትለውን ጉዳት በማስታወስ የአማካሪ ኮሚቴው በተጨማሪ በእኩልነት ፕሮግራሞች ለማግኘት እና የትምህርት ቤት ጥራት፣ የዳይቨርስቲ አስፈላጊነት እና የቤተሰቦች ትምህርት ቤት በግል ምርጫ የማስገባት ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ተመሳሳይ የትምህርት ቤት ምርጫ ሀሳብ ያቀርባል። እንደዚህ ያለ የአካባቢ ድልድል እና የትምህርት ቤት ምርጫ ለቤተሰቦች እና ለዲስትሪክቱ እንዲሠራ አማካሪ ኮሚቴው በተጨማሪ ከተማዋ ትምህርት ቤት የመክፈት፣ የመዝጋት እና የማግኘት እንዲሁም የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን እና ቻርተር ትምህርት ቤቶችን የማስፋፋት እና የመቀነስ ችሎታ እና የሚያወጣውን ገንዘብ እንዲገመገም እና እንዲያሻሽል ሀሳብ ያቀርባል። በመጨረሻም፣ አማካሪ ኮሚቴው በልጆች ቁጥር መብዛት ግፊቶች እና የማጓጓዣ ችግር ምክንያት አዳዲስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና ተጨማሪ ይዞታ የት እንደሚያስፈልጉ ለይቷል።

ለቤተሰቦች፣ ለትምህርት ቤቶች እና ለማህበረሰቦች ቀላል እና ውጤታማ ሽግግር ለማድረግ የታቀደው የተማሪ ድልድል ፖሊሲዎች፣ ወሰኖች፣ የዝውውር መንገዶች እና አዲስ ትምህርት ቤቶች ቀስ በቀስ በሥራ ላይ ይውላሉ።

# በክልል የተመደቡ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ዋና ሥርዓት

ማህበረሰቡን በማሳተፍ ሂደት ሥርዓት ላላቸው ትምህርት ቤቶች ጠንካራ ድጋፍ ያለ ይመስላል። ጂኦግራፊያዊ የትምህርት ክልሎች ተሳታፎን ማሻሻል እና ግልጽ ማድረግ የሚከተሉትን ያደርጋል፣

- ለቤተሰቦች በሁሉም የክፍል ደረጃ የተረጋገጠ መተላለፊያዎች መስጠት።
- ለትምህርት ቤቶች መሻሻል ለሚደረገው ጥረት በቤተሰቦች፣ ማህበረሰቦች እና ትምህርት ቤቶች ያለውን ግንኙነት ማጠናከር።

በ2013-14 ዓ.ም. 104 የተለያዩ ወሰኖች ውስጥ 74 የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከአንደኛ እና ከPS እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ አገልግሎት ሰጥተዋል። ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ እና ከተቀላቀሉ በኋላ የመመዝገቢያ ክልሎች ስላልተስተካከሉ ሀያ ሁለት በመቶ የሚሆኑት የሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ለመግባት መብት ነበራቸው። ብዙ ትምህርት ቤቶች ለየትኛው ማህበረሰብ ኃላፊ እንደሆኑ ግልጽ አይደለም፣ እንዲሁም ብዙ ቤተሰቦች ለየትኛው የትምህርት ቤት ዝውውር መብት እንዳላቸው ግልጽ አይደለም። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የትምህርት ቤት መመዝገቢያ ክልሎች በመቀላቀላቸው ምክንያት ቤተሰቦች ከቤታቸው በእግር ለመሄድ ቅርብ ባልሆነ ትምህርት ቤት ተመድበዋል። በተጨማሪም፣ አንዳንድ የትምህርት ቤት ወሰኖች ከሚገባ በላይ ተማሪዎች ሲኖራቸው አንዳንድ ወሰኖች ደግሞ ከተማሪዎች የበለጠ ቦታ አላቸው።

የተሻሻሉት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሳትፎ ወሰኖች የሚከተሉትን ይጠይቃሉ፣

- ቤተሰቦች ለትምህርት ቤት ያላቸውን መብቶች እና ትምህርት ቤቶች ለቤተሰቦች ያላቸውን ኃላፊነቶች ግልጽ ማድረግ፣
- የትምህርት ቤት ወሰኖችን በመጠን፣ በተሳትፎ እና በሕዝብ ብዛት ማመጣጠን።
- ለቤተሰቦች የመጓጓዣ ርቀትን መቀነስ።

በአሁኑ ጊዜ የመካከለኛ ትምህርት ቤት ወሰኖች ወደ እነሱ ከሚልኩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር አይመጣጠኑም፣ እንዲሁም ይህ እውነታ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ወደ እነሱ ለሚልኩ መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ነው። ይህም ማለት አንድ ልጅ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወሰን ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት ሊማር ይችላል፣ ሆኖም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ለሚሰደው መካከለኛ ትምህርት ቤት ከወሰን ውጭ ይሆናል። ወላጆች እና የማህበረሰብ ዓባሎች በአንድ ክፍል የተማሩ ልጆች አብረው በመዘዋወራቸው አጥብቀው ያምናሉ፣ እንዲሁም የትምህርት ሊቆች የአካዳሚ ፕሮግራሞች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ቀጥ ያለ ዘውውር ማየት እንደሚፈልጉ ምኞታቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ ልዩ ፕሮግራም ባላቸው ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች የሚማሩ ተማሪዎች ወደ መካከለኛ ወይም ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚሸጋገሩበት ጊዜ የአካደሚ ፕሮራማቸውን ለመቀጠል የተወሰነ እድል ነው ያላቸው።

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጂኦግራፊ የመማሪያ ክልል እና ዝውውር እንዲሁም የፕሮግራም ዝውውር ፓተርን እቅዶች የሚከተሉትን እንዲያካትቱ ይፈለጋል፣

- የአካዳሚ ፕሮግራሞች እንዲቀጥሉ መገፋፋት፣
- የፕሮግራም ቀጣይነት እና የምዝገባ ቋሚነትን መደገፍ የሚያስችል ትምህርት ቤቶች ከታች ወደ እላይ (አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ) ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር
- አንድ ትምህርት ቤት አብረው የተማሩ ተማሪዎች አንድ ላይ እንዲሆኑ መብት መስጠት፣
- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የበለጠ የኢኮኖሚ፣ የዘር እና የተለያየ ጎሳ እንዲኖር ማበረታታት።

| የዲሲ የክልል የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን በመብት ማግኘት ዕቅዶች | |
|---|---|
| 1. | እያንዳንዱ ተማሪ ለክፍሉ ተገቢ ትምህርት ቤት በመኖሪያው/ዋ መሠረት እንዲማር/ትማር መብት የሚሰጠውን አሁን ያለውን በክልል የመማር ፖሊሲ መቀጠል። |
| 2. | ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት በትምህርት ቤቶች መዘጋት እና መከፈት ምክንያት ከሥራ ውጭ የሆኑትንና ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ወሰኖች ማሻሻል። በትምህርት ቤት አዲስ የታቀዱትን ወሰኖች ለማየት እባክዎ በድህረ ገጽ dme.dc.gov/boundaries ይመልከቱ። |
| 3. | የመካከለኛ ትምህርት ቤት መማሪያ ክልሎች በጂኦግራፊ ወደ መካከለኛ ትምህርት ቤት ለማዘዋወር የተመደቡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የመማሪያ ክልሎችን በማቀላቀል ይመሠረታሉ። በትምህርት ቤት የተመደቡትን አዲሶቹን ወሰኖች በድህረ ገጽ dme.dc.gov/boundaries ይመልከቱ፣ ወይም በጂኦግራፊ ዝውውር መንገዶች የተወዱትን በዚህ ሰንድ መጨረሻ ይመልከቱ። |
| 4. | የሁለተኛ ደረጃ መማሪያ ክልሎች በጂኦግራፍ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማዘዋወር የተመደበ መካከለኛ ትምህርት ቤት ወይም ከ PS እስከ -8 ክፍል ክልሎችን በማቀላቀል ይመሠረታሉ። በትምህርት ቤት አዲስ የታቀዱትን ወሰኖች ለማየት እባክዎ በድህረ ገጽ visit dme.dc.gov/boundaries ይመልከቱ፣ ወይም የታቀደውን የጂኦግራፊ ዝውውር መንገዶች በዚህ ሰንድ መጨረሻ ይመልከቱ። |
| 5. | ተማሪዎች በተመደቡበት የመካከለኛ ትምህርት ቤት ክልል ይኑሩ ወይም አይኑሩ የዲሲ አንደኛ ደረጃ የሕዝብ ምህርት ቤቶች ተማሪዎች በጂኦግራፊ ዝውውር ፓተርን ቀጥሎ ለሚገቡበት መካከለኛ ትምህርት ቤት የመግባት መብት አላቸው። |

| | |
|---|---|
| 6. | ተማሪዎች በተመደቡበት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክልል ይኑሩ ወይም አይኑሩ የዲሲ መካከለኛ ደረጃ የሕዝብ ምህርት ቤቶች ተማሪዎች በጂኦግራፊ ዝውውር ፓተርን ቀጥሎ ለሚገቡበት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግባት መብት አላቸው። |
| 7. | የዲስ የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፕሮግራም ዝውውር ፓተርን ቀጥሎ ለተመደቡበት ደረጃ ልዩ ፕሮግራም/ትምህርት ቤት የመግባት መብት አላቸው። የታቀደውን ፕሮግራማዊ ዝውውር መንገዶች በዚህ ሰነድ መጨረሻ ይመልከቱ። |

## በዲስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የጨቅላ ልጆች ትምህርት ማግኘት

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት በጨቅላ ልጆች ሥልጠና መሪ ነው። እያንዳንዱ የዲሲ የመጀመሪያ ደረጃ ሕዝብ ትምህርት ቤት የሙሉ ቀን PK4 ክፍሎች ያስተምራል፣ እንዲሁም ከስድስት እስከ አንደኛ ደረጃ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በስተቀር ሁሉም የPK3 ክፍሎች አሏቸው። በአሁኑ ጊዜ የጨቅላ ትምህርት ፕሮግራም ለመግባት ቀደምትነት የሚሰጠው በፍላጎት ሳይሆን በሎተሪ እጣ ነው።

በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ቅድመ ኪንደጋርደን ፕሮግራሞች ለመግባት ዕቅዶቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

- በአስጊ ሁኔታ ላይ ላሉ ወጣት ተማሪዎች በኪንደርጋርደን እና ከዛም በላይ ጥሩ ውጤት ለማምጣት እንዲችሉ የሙብት ዕድሎችን መፍጠር።
- በአካባቢ ትምህርት ቤቶች የማያቋርጥ ምዝገባ እና ተሳትፎ የሚያበረታታ የቤተሰቦች ተሳትፎ መፍጠር።
- ለቤተሰቦች ለቤታቸው አቅራቢያ የሆነ አስተማማኝ በሙብት ዝውወር መፍጠር።

| በህጻነነት ጊዜ የሚሰጥ ትምህርትን የማግኘት ዕቅዶች | |
|---|---|
| 8. | በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ታይትል I የሚጠቃለሉ ትምህርት ቤቶች በ"የኔ ትምህርት ቤት ዲሲ." ሥርዓት እስከ PK3 እና PK4 በክላላቸው በሚገኝ የዲሲ ትምህርትቤት መቀመጫ የማግኘት መብት አላቸው። |
| 9. | በዲስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ታይትል I የማይጠቃለሉ ትምህርት ቤቶች ፕሮግራም በመኖር እና በቦታ መጠን እና በሚኖሩት የሎተሪ ምርጫዎች ለPK3 እና PK4 መቀመጫዎቻቸው በሎተሪ ዕጣ ይሰጣሉ። |

## መጓጓዣ ማግኘት

ጥራት ያለው ትምህርት ቤት ለማስገባት የሚፈልጉ ቤተሰቦች በዋጋ፣ በጊዜ እና አስጊ ያልሆነ መመላለሻ ችግር ምክንያቶች ወደ ትምህርት ቤት መሄድ መሰናከል ሊሆን ይችላል።

መጓጓዣ የማግኘት ዕቅዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

- የህዝብ መመላለሻ አገልግሎቶችን ማሻሻል እና ለህዝብ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች የገንዘብ አቅም ተመጣጣኝ ማድረግ።
- ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ እና የሚመለሱ ተማሪዎችን ደህነነት ማሻሻል።

| የማጓጓዝ ዕቅዶች | |
|---|---|
| 10. | የአውቶቡስ መንገዶችን እና ሌሎች ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ አስጊ ያልሆኑ መንገዶችን ለመገምገም እና ለዲሲ የህዝብ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች አግልግሎቶችን እና መንገዶችን ለማጣጣም እና እቅድ ለማውጣት የትምህርት ምክትል ከንቲባው ከሜትሮ፣ ከሜትሮፖሊታን እና ሜትሮ ፖሊስ፣ የዲሲ የትራንስፖርት መምሪያ እና የህዝብ ትምህርት ቤት ወላጆች እና ተማሪዎች ጋር መሥራት አለበት። |
| 11. | አንድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ክልሉ/ሏ የሚገኝ ትምህርት ቤት በእግር ለመድረስ ከአንድ ማይል እርቀት በላይ የሚወስድ ከሆነ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ ልጁን/ቷን ትምህርት ቤት ለማድረስ ነጻ የሜትሮ አውቶቡስ አገልግሎት ይሰጣል። |
| 12. | አንድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ክልሉ/ሏ የሚገኝ ትምህርት ቤት በእግር ለመድረስ በአንድ ማይል እርቀት ውስጥ የሚኖር ካልሆነ/ነች ተማሪው/ዋ በየኔ ትምህርት ቤት ዲሲ ሎተሪ የቅርበት የበላይነት ያገኛል/ታገኛለች። |
| 13. | ዲስትሪክቱ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ወደ ህዝብ ትምህርት ቤት ለመሄድ እና ለመመለሻ ነጻ የሜትሮባቡር አገልግሎት ይሰጣል። |

# ተመጣጣኝ የትምህርት ቤት ምርጫዎች ሥርዓት

## የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከወሰን ውጭ ፖሊሲ

በአሁኑ ጊዜ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ቤተሰቦች በመግሪያ ክልል፣ በዝውውር መንገድ፣ ወይም በሎተሪ በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እንዲገቡ ያደርጋል። ሆኖም፣ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ውጤት ያላቸው የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሁልጊዜም ለጀማሪ ደረጃ ክፍሎች በሎተሪ ጥቂት መቀምጫዎች ብቻ ይኖራቸዋል። ወላጆች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የአካባቢ ትምህርት ቤቶች እንዲኖራቸው ታላቅ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል፣ ሆኖም ከክልላቸው ውጭ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ማግኘት እንዲችሉም ፍላጎታቸውን ገልጽዋል። ከወሰን ውጭ የሎተሪ ዕቅድ የሚከተሉት እንዲፈጸሙ ይጠይቃል፣

- ቤተሰቦች ለልጆቻቸው የሚስማሙ ወይም ለቤተሰቦች አመቺ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ማስገባት እንዲችሉ ማድረግ።
- በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች አካባቢ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ዳይቨርስቲ እንዲጨመሩ እና እንዲጠበቁ።
- "በአደጋ ላይ ያሉ" ተማሪዎች ከፍተኛ ተፈላጊነት ባላቸው የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ክልል ለመግባት የተሻለ እድል እንዲኖራቸው ማድረግ።

| በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከወሰን ውጭ ፐሊሲዎች ዕቅዶች |
|---|
| 14. ከ2015 -16 ጀምሮ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ቢያንስ 10 በመቶ መቀመጫዎች ከክልል ውጭ ለሆኑ ተማሪዎች በክልል ውስጥ ባሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይመድባል። |
| 15. ከ 2015-16 ጀምሮ በተማሪ አንድ ዓይነት የሆነ የገንዘብ እርዳታ ፎርሙላ (UPSFF) "በአደጋ ላይ ያሉ" ተብሎ የተሰየሙ ተማሪዎች ቁጥር 30 በመቶ ወይም ያነሰ ያላቸው የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች "በአደጋ ላይ ያሉ" ተማሪዎች በሎተሪ እጣ ቀደምትነት ይሰጣል። |
| 16. የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በክልል ውስጥ የሚገኙ መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ቢያንስ 10 በመቶ የ6ኛ ክፍል መቀመጫዎች የመዘዋወር መብት ለሌላቸው ከክልል ውጭ ላሉ ተማሪዎች ይመድባል። ሥራው በ2018-19 የትምህርት ዓመት ይጀምራል። |
| 17. የዲሲ ትምህርት ቤቶች በክልል ውስጥ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከአዲሱ 9ኛ ክፍል መቀመጫዎች (9ኛ ክፍል የደገሙትን ሳይጨምር) ቢያንስ 10 በመቶ የዝውውር መብት ለሌላቸው ከክልል ውጭ ላሉ ተማሪዎች ይመድባል።ሥራው በ2018-19 የትምህርት ዓመት ይጀምራል። |
| 18. ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ሎተሪ ጀምሮ፣ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች PK3/4 DCPS ሎተሪ ቀደምትነቶች፣ በቅደመ ተከተል የሚከተሉት ይሆናሉ፣<br>• በወሰን ውስጥ ከወንድም ወይም እህት ጋር<br>• በውሰን ውስጥ<br>• ከወሰን ውጭ ከወንድም ወይም እህት ጋር<br>• ከወሰን ውጭ "በአደጋ ላይ ያሉ" (ብቁ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ብቁ ለሆኑ ተማሪዎችን) **<br>• ከወሰን ውጭ ከቅርበት ጋር (ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች) **<br>(** አዲስ ፖሊስዎችን ያመለክታል) |
| 19. ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ሎተሪ ጀምሮ፣ K-12 የዲስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ቀደምትነቶች፣ በተራ የሚከተሉት ይሆናሉ፣<br>• ከወሰን ውጭ ከወንድም ወይም እህት ጋር<br>• ከወሰን ውጭ "በአደጋ ላይ ያሉ" (በቁ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ብቁ ለሆኑ ተማሪዎችን) **<br>• ከወሰን ውጭ ከቅርበት ጋር (ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች) **<br>(** አዲስ ፖሊስዎችን ያመለክታል) |

## የዲሲ ትምህርት ቤቶች ልዩ ትኩረት ያላቸው እና ምርጥ ትምህርት ቤት ፖሊሲዎች

ልዩ ትኩረት ያላቸው እና ምርጥ ትምህርት ቤቶች በአካባቢ-ክልል በሚገኙ አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መኖር ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ አለው። በአሁኑ ወቅት የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ስድስት በምርጫ መመዝገቢያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ሁለት ከተማ አቀፍ የሎተሪ ልዩ ፕሮግራም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ልዩ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች አሉት።

ልዩ ትኩረት ያላቸው እና ምርጥ ትምህርት ቤቶች ዕቅድ የሚከተሉትን ይጠይቃል፣

- የአካባቢውን የመብት ትምህርት ቤቶች ጥያቄ ከግምት በማስገባት ልዩ ትኩረት ያላቸው ፕሮግራሞች አቀማመጥ አግባብነቱን ማረጋገጥ።
- ልዩ ትኩረት ፕሮግራም ክልል ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች ለልጆቻቸው የተሻለ ተስማሚ አማራጭ ፕሮግራሞች እንዲያገኙ ማድረግ።

| ለልዩ እና ለተመረጡ ትምህርት ቤቶች ንድፈ ሀሳቦች |
| --- |
| 20. የሚከተለውን ልዩ ትኩረት ያለው ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ትርጉም ይጠቀሙ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ያለ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ሥረዓተ ትምህርቱ ወይም የማስተማር ዘዴው ከዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መደበኛ ክፍል ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተለየ፣ እንደ ልዩ የአስተማሪ ሥልጠና እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በሁሉም ክፍሎች እና ሁሉም ያንን ፕሮግራም ከሚሰጡ ክፍሎች (ለምሳሌ፣ ሁለት ቋንቋ፣ ሞንትሶሪ፣ ሬጅዮ እሚሊያ) የተለየ። |
| 21. የተለዩ (ምርጫ የማያደርጉ) ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ክፍል ለማገልገል በቂ ቦታ ያላቸው በቅርብ የሚገኙ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከሌሉ በስተቀር በስተቀር ወሰን ያላቸው የአካባቢ ትምህርት ቤቶች መሆን ይኖርባቸዋል። |
| 22. የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ለተለየ ወሰን ክልል ተማሪዎች ቦታ ከፈለገ፣ በእዛ ወሰን ውስጥ የሚገኙ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤቶች--- ሎተሪ ወይም ምርጥ ትምህርት ቤቶች -- የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል፣<br>• በእዛ አካባቢ ለሚገኙ ተማሪዎች ቦታ ለመልቀቅ ወደ ሌላ ቦታ መዘዋወር፣ ወይም<br>• ወደ የአካባቢ ትምህርት ቤት መለወጥ እና ልዩ ትኩረት ካለው ፕሮግራም ጋር ልዩ ትኩረት የሌለው የሌለው ፕሮግራም መስጠት። ወይም<br>• የአካባቢ ትምህርት ቤት በመለወጥ እና የተለመደ ደረጃ ክፍልፕሮግራም ለመስጠት ልዩ ፕሮግራም ከሌለው ትምህርት ቤት ጋር ማጣመር። ወይም<br>• በከተማ አቀፍ ሎተሪ የአካባቢ ቀደምትነት መስጠት። |
| 23. የሁለት ቋንቋ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ትምህርት ቤት አካባቢ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች ሁለት ቋንቋ የሌላቸው የተመደቡ የክልል ልዩ ትምህርት ቤት አማራጭ ትምህርት ቤቶች የመግባት መብት ይኖራቸዋል። |
| 24. የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች በልዩ ፕሮግራሞች፣ በምርጫ፣ ወይም የቻርተር ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም በዲሲ ነዋሪ ተማሪዎች ቦታ እንዳይመደቡ ያረጋግጣል። |

## የተማሪዎች መቀጠል እና መዘዋወር ፖሊሲዎች

የተማሪዎች በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል የመዘዋወር መጠን ለተማሪዎች እና ትምህርት ቤቶች ችግር ይፈጥራል። በተደጋጋሚ ትምህርት ቤት የሚለውጡ ተማሪዎች በስታትስቲክስ አነስተኛ ከትምህርት ቤት ምረቃ እና መጥፎ ወጤቶች ያሳያል። በተጨማሪም፣ በትምህርት ቤት የምዝገባ እና ቁሳቁሶች ላይ የሚያስከትለው ሌሎች ተማሪዎች ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል። አሁን ያለው የተማሪ ድልድል እና ምርጫ ፖሊሲዎች የተማሪዎች መዘወዋወር የሚያመጣውን ተጽእኖ ሚዛን ውስጥ አያስገባም፣ እንዲሁም ይህንን ዝውውር ለማስቀም ቅጣት የለም።

የተማሪዎች መቀጠል እና መዘዋወር ዕቅዶች የሚከተሉትን ያጠቃልላ፣

- ቤተሰቦች በትምህርት ዓመት ውስጥ መዘዋወርን እንዲቀንሱ ማበረታቻ መስጠት።
- መቀጣት ያለባቸው ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ጋር ቅርበት እንዲኖራቸው ፍላጎታቸውን የሚያሟላ ዕድሎችን መስጠት።
- ተማሪዎች ዝውውርን እንዲያቆሙ እና በትምህርት ገበታ ላይ እንዲቆዩ ድጋፍ የመስጠት ፖሊሲዎችን እና አሠራሮችን ማበረታታት።
- በአደጋ ላይ ያሉ ተማሪዎች ትርጉም ያለው ምርጫ ማግኘት እንዲችሉ ማረጋገጥ።

| የተማሪዎች መዘዋወር ፖሊሲዎች ዕቅዶች |
| --- |
| 25. አንድ ተማሪ በዲሲ ውስጥ የመኖሪያው ቦታ ከአንድ የትምህርት ቤት ክልል ወደ ሌላ የትምህርት ቤት ክልል ከተለወጠ/ች የትምህርት ዓመቱ እስከሚያልቅ ድረስ አሁን ያለበት/ችበት ትምህርት ቤት እንዲቆይ/ትቆይ ይፈቀድለታል/ላታል፣ እንዲሁም በአደጋ ላይ ያሉ ተብለው የተሰየሙ ተማሪዎች እስከ መጨረሻ ክፍል ደረጃ ድረስ ትምህርት ቤቱ እንዲማሩ ይፈቀድላቸዋል። |
| 26. ከተማዋ አግባብ ካላቸው ደንበኞች (የዲስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የዲሲ የህዝብ ቻርተር ቦርድ፣ የአካባቢ የምህርት ቻርተር ኤጀንሲዎች (LEAs) እና የማህበረሰብ እና የተማሪ ተወካዮችን ጨምሮ) ጋር የሚከተሉትን ለማድረግ አብሮ መሥራት ይኖርባታል፣<br>• ከፍተኛ የዝውውር ቁጥር የሚኖርበትን ምክንያት አጥንቶ የፖሊሲ እና የፕሮግራም አስተያየቶችን ማዘጋጀት፣<br>• ስለ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት መባረር፣ ማቋረጥ እና በዓመቱ አጋማሽ ያለፈቃድ ከትምህርት ቤት መዘዋወር ሁኔታዎችን መነጋገር። እና<br>• ለዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች በዓመቱ አጋማሽ ለሚደረጉ መባረሮች እና የረዥም ጊዜ እገዳዎች የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የምርጫ ፕሮግራምን ወደ ሴክተር ተሻጋሪ ፕሮግራም ለማሳደግ ያለውን እድል መመርመር። |

# የተማሪ ድልድል ለውጦችን በሥራ ላይ ማዋል

ማንኛውም የወሰን ወይም የዝውውር ለውጦች በሥራ ላይ የሚውሉበት የመጀመሪያው ዓመት በ2015-16 የትምህርት ዓመት ነው። ሆኖም፣ የወሰን እና የዝውወር ለውጦች የተደረገበት ምክንያት ለቤተሰቦች እና ለዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በቂ የመሸጋገሪያ ጊዜ እንዲኖር ለማረጋገጥ ነው።

## የፖሊሲ፣ ወሰን እና የዝውውር ለውጦች እቅዶች

ሀ. ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ጀምሮ በወሰናቸው ውስጥ ተመድበው የነበሩ ተማሪዎች እና ወንድሞቻቸው ወይም እህቶቻቸው ግን ወደሌላ ትምህርት ቤት ክልል የተዘዋወሩ ከትምህርት ቤቱ ጨርሰው እስከሚወጡ ድረስ በአሁኑ የወሰን ውስጥ ትምህርት ቤት የመቀጠል መብት አላቸው።

ብ. ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ጀምሮ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ክልል የተዘዋወሩ አዲሱ ክልል ትምህርት ቤት የማማር መብት አላቸው።

ለ. ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ጀምሮ ሁሉም **አዲስ ተማሪዎች** ወደ አዲሱ ክልል ትምህርት ቤት ይመደባሉ። አዲስ ተማሪዎች በሚከተለው ይገለጻሉ፣

- ለሌላ ትምህርት ቤት የተመደበ አካባቢ የተደለድሉ ተማሪዎች።
- የቻርተር ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወይም ከወሰን ውጭ የዲሲ ህዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ከቻርተር ትምህርት ቤታቸው ወይም ከወሰን ውጭ ያለ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ወደ የአካባቢያቸው የዲሲ ህዝብ ትምህርት ቤቶች መመለስ የሚፈልጉ ተማሪዎች።
- ለመጀመሪያ ጊዜ ትምህርት ቤት የገቡ (ለምሳሌ፡ የመጀመሪያው ክፍል) እንደገና ወደ ተከለለ አካባቢ የሚኖሩ እና የመጀመሪያው ድልድል ትምህርት ቤት ውስጥ ወንድም ወይም እህት የሌላቸው ተማሪዎች።

ሐ. ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ጀምሮ PK3 እና PK4 ተማሪዎች በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ክልል በሚገኝ አንደኛ ደረጃ ወይም ከPS እስከ 8ኛ ክፍል ያለ ትምህርት ቤት የታይትል I እስከሆነ ድረስ መግባት ይችላሉ። ሆኖም የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለሠራተኛ፣ ቁሳቁስ እና ቦታ ዕቅድ ለማውጣት እንዲችሉ በየኔ ትምህርት ቤት ዲሲ የመመዝገቢያ ማብቂያ ቀን መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

መ. ለ2014-15 የትምህርት ዓመት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ3ኛ እስከ 5ኛ ክፍል ለገቡ እና የዝውውር ፓተርናቸው የተለወጠ የበፊቱ ትምህርት ቤታቸው ወይም አዲስ የተመደቡበት ትምህርት ቤት ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ጀምሮ መግባት ይችላሉ።

ሰ. ከPK3 እስከ 2ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከ2014-15 የትምህርት ዓመት ጀምሮ በልውውጡ ጊዜ የበፊቱ ትምህርት ቤት የሚማሩ ወንድሞች ወይም እህቶች እስከሌላቸው ድረስ ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ይዘዋወራሉ።

ረ. ለ2014-15 የትምህርት ዓመት ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዝውውር ንገድ የሚለወጥ ከሆነ በ2015-16 የትምህርት ዓመት በቀድሞው የዝውወር መንገድ ወይም በተመደበው በአዲሱ መንገድ የመቀጠል መብት አላቸው።

ሠ. አዲሱ የዝውውር መንገዳቸው አዲስ ትምህርት ቤት በመከፍት ላይ የተመሠረተ ከሆነ አዲሱ ትምህርት ቤት እስከሚከፈት ድረስ በአሁኑ የዝውውር መንገድ እና የጂኦግራፊያዊ መብቶቻቸው መቆየት ይችላሉ።

ሸ. ከ2018-19 የትምህርት ዓመት ጀምሮ የታቀደው 10 ከመቶ ከወሰን ውጭ ላሉ መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ለ6ኛ ክፍሎች የተቀመጡ በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤቱ የዝውውር ፓተርን ውስጥ አስቀድመው ላልገቡ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በሎተሪ እጣ ይሰጣሉ።

ቀ. በ2018-19 የትምህርት ዓመት ጀምሮ የታቀደው 10 ከመቶ ከወሰን ውጭ ላሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ለ9ኛ ክፍሎች የተቀመጡ በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤቱ የዝውውር ፓተርን ውስጥ አስቀድመው ላልገቡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በሎተሪ እጣ ይሰጣሉ።

# ግልጽ የሆነ ከፍተኛ ጥራት ያለው የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሥርዓት

## በህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እና ከዳር እስከ ዳር የተሻለ ዕቅድ

በዚህ ሂደት ውስጥ የማያቋርጥ አርዕስት – በህዝብ ስብሰባዎች እና በአማካሪ ኮሚቴ ስብሰባዎች – በከተማ አቀፍ የተማሪዎች ድልድል ጥረት የአካባቢ የቻርተር ትምህርት ቤቶች ያላቸውን ቦታ መመልከት ነበር። ቢ.ዲ.ሲ. ቻርተር ትምህርት ቤቶች የተፈጠረውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ ለዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ድልድል ፖሊሲዎች መፍጠር በመላው በዲስሪክቱ ለሚገኙ ቤተሰቦች እርግጠኛንትን እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ትምህርት ቤቶች ማግኘትን በትክክል እንደማይመለከት ሰፋ ያለ ተቀባይነት ነበርወ።

ስለቻርተር ተጠያቂነት እና እድገት በሥራ ቡድን ተካፋዮች ጥርጣሬ ነበር፣ አብዛኞቹ በቻርተር ምዝገባ ላይ ከተማ አቀፍ ጣሪያ እንዲኖር ምርጫ እንዳላቸው ስሜታቸውን ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ፣ ተሳታፊዎች የእያንዳንዱን አካባቢያዊ የትምህርት ኤጀንሲ የህዝብ ቻርተርን መሠረታዊ የትምህርት ሥልጣን ዝቅ ማድረግ አልፈለጉም።

ከሁሉም በላይ ስለ ዕቅዱ የነበሩ ስጋቶች በሴክተሮች መካከል የነበሩ የቅንጅት ጉድለቶች ብቻ አልነበሩም፣ ስለሆነም በትምህርት ቤት ወሰኖች፣ የትምህርት ቤቶች መዘጋት፣ እንዲሁም ለዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች አቅርቦቶች የካፒታል እቅድ ውሳኔ መስጠት ላይ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ውስጣዊ የማቀድ አቅም ጉድለትም ጭምር ነበር።

የዲስትሪክቱን በህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ እና ባጠቃላይ ዕቅድ የማሻሻል አስተያየት የሚከተሉትን ይጠይቃል፣

- ለቤተሰቦች የበለጠ ዘላቂ እና ትክክለኛ የሆኑ የከተማ ሪሶርሶች እና ዕድሎች የሚያስገኙ ሁኔታዎችን መፍጠር።
- የትምህርት ቤት አቅርቦት/ፍላጎት ጉዳዮች ላይ፣ የትምህርት ቤት አካባቢዎችን መወሰን እና የተማሪ ድልደላ መመሪያዎች ላይ ፈተናዎችና መፍትሄዎችን ለመለየት የተረዳ፣ ግልጽ፣ በህዝብ ይፋ የሆነ ሂደትን ማበረታታት።

| ለትምህርት ህንጻዎች ፕላን ማውጣት እቅዶች |
| --- |
| 27. በ2022 እና ከዛ በኋላ በየአስር ዓመታት ከተማዋ አጠቃላይ የተማሪ ድልድል ግምገማ ፖሊሲዎችን፣ የትምህርት ቤቶች ወሰኖችን እና የዝውውር ፓተርኖችን የተመለከተ ጨምሮ አጠቃላይ ግምገማ ታደርጋለች። |
| 28. ቻንስለሩ በእያንዳንዱ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዝውውር መንገድ ትኩረት ባላቸው እና የምርጫ ፕሮግራሞች ተመሳሳይነት መኖሩን ያረጋግጣል። |
| 29. ቻንስለሩ የትምህርት ዕቅድን በተመለከተ በእያንዳንዱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት ያላቸው እና የምርጫ ፕሮግራሞች መኖራቸውን እና ድጋፍ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። |
| 30. በሁለቱ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መረጃዎችን መካፍልን እና ትብብርን በተመለከቱ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ከተማዋ እና የሚመለከታቸው ተጠቃሚዎች በሚመለከቱት ላይ መነጋገር ይኖርባቸዋል፣<br>• የህዝብ ትምህርት ቤቶች መከፈት እና መስፋፋት፣ መዘጋት፣ መዘዋወር፣<br>• የካፒታል ፕሮግራም ኢንቬስትመንት<br>• የክፍል አደረጃጀቶች ስምምነት<br>• በህዝብ ትምህርት ቤቶች "በአደጋ ላይ ያሉ" ተማሪዎች ድልድል<br>• በትምህርት ዓመት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር የተማሪዎች በትምህርት ቤቶች መካከል መዘዋወር |
| 31. በዝውውር ፓተርኖች ለውጦች አንድ ዓይነት የህዝብ ማስታወቂያ እና የተሳትፎ ጥያቄዎች መኖሩን ለማረጋገጥ ከተማዋ የዲሲ ሙኒሲፓል ድንጋጌን መገምገም አለባት። |

## የሙብት ትምህርት ቤቶችን ድጋፍ የሚሰጥ በቂ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ችሎታ መኖሩን ማረጋገጥ

የልጆች ቁጥር መጨመር ወይም መቀነስ በዋናነት በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚጣል ሲሆን እንደ የማዘጋጃ ቤት ሥርዓት ሙብት ይቆጠራል። ሁሉም የግዴታ ትምህርት ተማሪዎች፣ ከየትኛውም ቦታ፣ ፍላጎት፣ በትምህርት ዓመቱ መቼ እንደገቡ ከግምት ሳይገባ፣በዲስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መገልገል አለባቸው። ይህንን ግዴታ ለሚሟላት ዲስትሪክቱ አሁን ካለው እና ለወደፊት ከሚገመተው የተማሪዎች ፍላጎቶች እና ከዲስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የካፒታል ዕቅድ ጋር የሚጣጣም ዕቅድ ማውጣት ይኖርበታል። አሁን ካለው እና ከሚገመተው የልጆች ተማሪዎች ብዛት አንጻር የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለተጨመረው የሙብት ትምህርት ቤቶች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀት አለበት።

የትምህርት ቤት ህንጻ ይዞታ ዕቅዶች የሚከትሉትን ያካትታል፣

- የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለዲስትሪክቱ ቤተሰቦች ለአሁን እና ለወደፊቱ የፕሮግራም እና የቦታ ፍላጎቶች አሁኑኑ ዕቅድ እንዲያወጣ ማረጋገጥ።
- በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ደረጃ የመጣበብ ወይም ሙሉ በሙሉ ያለመጠቀም ሁኔታዎችን በተመለከተ በአካባቢዎች ላይ ያተኮረ ዕቅድ ማውጣት።

| በቂ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ይዞታ መኖር ማረጋገጥ ዕቅዶች |
| --- |
| 32. የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በታይትል 1 ትምህርት ቤቶች የተስፋፋውን የPK3 እና PK4 መብቶች ከመደገፍ አንጻር የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ክልል ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦችን ለማስተናገድ የፕሮግራም እና የህንፃዎች ዕቅድና በጀት ማዘጋጀት ይኖርበታል። |
| 33. የሚከትሉትን ለማካሄድ የካርዶዛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መካከለኛ ክፍል ፕሮግራምን ለመተካት የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እራሱን የቻለ የመሀል ከተማ መካከለኛ ትምህርት ቤት መክፈት አለበት።በዋርዶች 1 and 2 ለሚኖሩ ቤተሰቦች የመካከለኛ ክፍል ትምህርትን እና ፕሮግራም ማሻሻል።<br>◆ የካርዶዛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ይዞታ። እና<br>◆ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ካርዶዛ ላኪዎች ጠንካራ መካከለኛ ክፍሎች መፍጠር። |
| 34. የሚከተሉትን ለማድረግ በማክፋርላንድ ደቡብ ዋርድ መካከለኛ ትምህርት ቤት ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ያልቀደመ መክፈት እና በአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያሉትን መካከለኛ ክፍሎች መዝጋት።<br>◆ የመካከለኛ ክፍል ትምህርቶችን እና ፕሮግራሞችን ማሻሻል።<br>◆ በአካባቢው ባሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሁን ያለውን እና የወደፊት መጣበብ ማስቀረት።<br>◆ የጨቅላ ልጆች በአካባቢ ትምህርት ቤቶች መግባት መስፋፋትን መደገፍ፣ እና<br>◆ የሁለት ቋንቋ መካከለኛ ትምህርት ቤት ዝውውር መስጠት። |
| 35. የሚከትሉትን ለማካሄድ በደቡብ ዋርድ 4 ከበጋ 2015 በፊት መካከለኛ ትምህርት ቤት ለመክፈት ቦታ መጠቆም እና በደቡብ ዋርድ 4 መከከለኛ ትምህርት ቤት ለመክፈት ማቀድ እና በአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያሉትን መካከለኛ ክፍሎች የኩሊጅ ሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤትን ከማደስ (2017-18) ጋር አያይዞ መዝጋት፣<br>◆ የመካከለኛ ክፍል ትምህርቶች እና ፕሮግራሞችን ማሻሽል፣<br>◆ በተለይ በብሪይትውድ እና ላ ሳሌ ትምህርት ቤቶች አሁን ያለውን እና የወደፊት መጣበብ ለማስቀረት፣ እና<br>◆ የጨቅላ ልጆች በአካባቢ ትምህርት ቤቶች መግባት መስፋፋትን መደገፍ። |
| 36. የሚከትሉትን ለማድረግ በሮን ብራውን ትምህርት ቤት የዋርድ 7 ትኩርት ያለው እና የምርጫ ፕሮግራም መካከለኛ ትምህርት ቤት ከ2015-16 የትምህርት ዓመት ያልቀደመ መክፈት፣<br>◆ ከኢስት ኦፍ ዘ ሪቨር የሚገኙትን የመካከለኛ ክፍል ትምህርቶች እና ፕሮግራሞችን ማሻሻል፣<br>◆ በከተማዋ የምርጫ ፕሮግራሞችን በእኩልነት ማከፋፈል፣<br>◆ በኬሊ ሚለር ያለውን መጣበብ ማስወገድ፣ እና<br>◆ ወደ ውድሰን ትምህርት ቤት የሚዘዋወሩ በደንብ የተዘጋጁ ተማሪዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ በውድሰን ዝውውር መንገዶች ኢንቨስትመንት መጨመር። |
| 37. የሚከተሉት ከተከሰቱ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች አዲስ ትምህርት ቤት ለመክፈት ወይም የክልል ትምህርት ቤቶችን ይዞታ ለማስፋፋት ጥናት ማድረግ አለባቸው፣<br>◆ በትምህርት ቤት ክልሎች ውስጥ አንደኛ ደረጃ የክልል ትምህርት ቤቶች ይዞታ ከተመጣጣኝ ዕድሜ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪ ቁጥር ጋር እኩል ወይም 45 ከመቶ በታች ከሆነ፣ እና<br>◆ በወሰን ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር 75 ከመቶ የበለጠ ወይም እኩል ከሆነ፣ እና<br>◆ የአንደኛ ደረጃ የክልል ትምህርት ቤቶች ጥቅም ላይ መዋል 90 ከመቶ ወይም በላይ ከሆነ፣ ወይም<br>◆ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በጂኦግራፊ ገለልተኛ ከሆነ እና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዕድሜ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ አስቸጋሪ ከሆነ። |

ከላይ በተጠቀሱት መስፈርቶች መሠረት፣ የአማካሪ ኮሚቴው በርካታ የሆኑ ትምህርት ቤቶች እንደገና ለመክፈት ያስባል።

- በታቀደው የሄንድሊ ወሰን፣ በሂንድሊ ትምህርት ቤት 32 ከመቶ የአንደኛ ደረጃ ዕድሜ ያላቸው በወሰኑ ውስጥ የሚኖሩ ልጆችን ብቻ የሚያስተናግድ ይዞታ ነው ያለው። የትምህርት ቤቱ የአሁን ይዞታ 101 ከመቶ ሲሆን፣ 91 ከመቶ በወሰን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። በሄንድሊ ወሰን ውስጥ የሚኖሩትን በቴሰቦች በቂ በሆነ መንገድ ለማገልገል የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ፍሪቢ-ሆፐ ትምህርት ቤትን እንደገና እንዲከፍት የአማካሪ ኮሚቴ አስተያየቱን ይሰጣል። የኪንሊወርዝ ማህበረሰብ ገለልተኛ ነው። አዲሱ ምድብ ቶማስ (ዋርድ 7) ትምህርት ቤት ለተማሪዎች በእግር የሚኬድበት አይደለም እንዲሁም ቶማስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገባው በላይ የተጣበበ ነው። 104 ከመቶ በጥቅም ላይ ውሏል። የአማካሪ ኮሚቴው የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ኪንልዎርዝ ትምህርት ቤትን (ዋርድ 7) እንደገና እንዲከፍት አስተያየት ያቀርባል።
- ማርሻል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 5) በአነስተኛ የተማሪ ቁጥር ምክንያት ተዘግቶ ነበር። ሆኖም በማደግ ላይ ያለ ገለልተኛ ማህበረሰብ ነው። በአሁኑ ጊዜ ማርሻል ትምህርት ቤት እንዲከፈት አማካሪ ኮሚቴው ሀሳብ አያቀርብም። ሆኖም፣ የማህበረሰቡን የልጆች ቁጥር እድገት በቅርብ እንዲከታተለው አስተያየት ያቀርባል።

38. የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የክልል ትምህርት ቤቶችን ይዞታ የመጨመር ወይም ወሰኖችን የማጥበብ ጥናት በቀደምትነት ማካሄድ አለበት፣
   - የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቱ 90 ከመቶ በጥቅም ላይ ውሎ ከሆነ ወይም በወሰን ውስጥ ያለው የተማሪ ቁጥር ለሦስት ዓመታት 75 ከመቶ በላይ ከሆነ፣
   - የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በየትምህርት ቤቱ ወሰን ያለውን የህዝብ ቁጥር፣ የዝውውር ትምህርት ቤቶች ምዝገባ፣ በወሰን ውስጥ ያለውን የተሳትፎ ብዛት፣ በአቅራቢያው ያለ ቻርተር ትምህርት ቤት ምዝገባ እና የህዝብ ግምትን ለመገምገም ከትምህርት ቤቶች እና ከማህበረሰቡ ጋር መሥራት አለበት።

በ2013-14 የትምህርት ዓመት እነኝህን መስፈርቶች የሚያሟሉ አንደኛ ደረጃ እና PS-8 ትምህርት ቤቶች የሚከተሉት ናቸው፤

| | | |
|---|---|---|
| ሄንድሊ አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 8) | ፕላመር አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 7) | ጄኒ አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 3) |
| ሳቮይ አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 8) | ትሩስዴል EC (ዋርድ 4) | ሙርች አደኛ ደረጃ (ዋርድ 3) |
| ፓተርሰን አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 8) | ላፊያት አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 4) | ስቶደርት አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 3) |
| ስታንተን አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 8) | ኪይ አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 3) | |

የአማካሪ ኮሚቴው እነኝህ ትምህርት ቤቶች የኢጋጠሟቸውን እክሎች የክፍል አደረጃጀት ለውጦችን፣ የወስን ለውጦችን እና የህንጻ ይዞታ መጨምርን በማመዛዘን ተመልክቶታል።


39. የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ፣ የዲሲ ህዝብ ትምህርት ቤቶች ከይዞታ በታች ጥቅም ላይ መዋልን ጥናት ቀደምትነት መስጠት ይኖርብታል፣
   - የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በተከታታይ ለሶስት ዓመታት 60 ከመቶ ወይም በታች ጥቅም ላይ ከዋሉ፣
   - የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ነክ የወሰን ተማሪዎች፣ የወሰን ውስጥ ተሳትፎ ብዛት፣ በአካባቢው ያለው የቻርተር ትምህርት ቤት ምዝገባ፣ የወሰኑ እና የአካባቢው ከአምስት እስከ አስር ዓመት የህዝብ ቁጥር ግምት፣ እንዲሁም ትምህርት ቤት መጠቀምን የሚያዳግቱ **ማንኛውም ዓይነት የትምህርት ቤት ጥራት እክሎችን ለመጠቆም** ከአካባቢው ትምህርት ቤት እና ማህበረሰብ ጋር መሥራት አለበት። እነዚህን አነስተኛ አጠቃቀሞች ለመከታተል የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በወሰኖች፣ አካባቢዎች፣ የክፍል አደረጃጀት ለውጦች ወይም የትምህርት ቤት ጣልቃ ገብነቶች ላይ እርምጃ መወሰድ አስፈላጊ መሆኑን መጠቆም አለበት።

በ2013-14 የትምህርት ዓመት እነዚህን መስፈርቶች ያሟሉ አንደኛ ደረጃ እና PS-8 ትምህርት ቤቶች የሚከተሉት ናቸው፣

| | |
|---|---|
| አይተን አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 7) | ብራውን EC ዋርድ 5) |
| ላንሊይ EC (ዋርድ 5) | ማልኮም ኤክስ (ዋርድ 8) |
| ብሩክላንድ በንከርሂል (ዋርድ 5) | ድርው አንደኛ ደረጃ (ዋርድ 7) |


የአማካሪ ኮሚቴው የእነዚህን ትምህርት ቤቶች ወሰኖችን በመጨመር እና የጨቅላ ልጆች መቀመጫዎችን ለማስፋፋት ምክር በመስጠት፣ በጊዜ ከቤተሰቦች እና ልጆች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ ግንኙነቶች አንድ ከተፈጠሩ የበለጡ ቤተሰቦች በአካባቢያቸው ባለ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይቀጥላሉ ብሎ በማሰብ እነኝህን ሁኔታዎች ለመከታተል ሞክሯል።

# የታቀደው የመካከለኛ ትምህርት ቤት መመዝገቢያ ክልል እና የጂኦግራፊ መዛዋወሪያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች




ያስታውሱ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የመመዝገቢያ ክልሎች በሰኔ 12 ረቂቅ መሠረት ነው። ወደ ተወሰኑት የመካከለኛ ትምህርት ቤቶች እንዲያሸጋግሩ የተመረጡት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ አይነት ናቸው። ለምሳሌ አም አይዶን በውን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ብሬትን አንደኛ ድረጃ ትምህርት ቤት፣ ታይለር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ቫኔስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ወደ ጀፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲልኩ የታቀደ ሲሆን እነሱም አንድ ዓይነት በሆነ በቡናማ ቀለም ተቀልመዋል።

# የታቀደው የሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት መመዝገቢያ ክልል እና የጂኦግራፊ መዘዋወሪያ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች




ያስታውሱ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የመመዝገቢያ ክልሎች በሰኔ 12 ረቂቅ መሠረት ነው። ወደ ተወሰኑት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲያሸጋግሩ የተመረጡት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ አይነት ናቸው። ለምሳሌ ሶሳ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ክሬመር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን ወደ አናኮስቲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲልኩ የታቀደ ሲሆን እነሱም አንድ ዓይነት በሆነ በደማቅ ጨለማማ ፒንክ ቀለም ተቀልመዋል።

# የታቀደው የጂኦግራፊ ዝውውር መንገዶች

የዝውውር መንገዶች የጂኦግራፊ፣ ፕሮግራም እና አካዳሚ መቀጠልን እና ማግኘትን ለመስጠት የተመሠረቱ ናቸው። በተጨማሪም የዲስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ብዛትን እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በይዞታ ልክ አለመጠቀምን አሠራር የሚመለከት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| **አናኮስትያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 8)** | | |
| ከችምን አንደኛ ደረጃ | ክሬመር መከከለኛ ትምህርት ቤት | አናኮስትያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ሞተን አንደኛ ደረጃ | | |
| ኦርr አንደኛ ደረጃ | | |
| ራንድል ሀይላንድስ አንደኛ ደረጃ | | |
| ሳቮይ አንደኛ ደረጃ | | |
| ስታንተን አንደኛ ደረጃ | | |
| ቢርስ አንደኛ ደረጃ | ሱሳ መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ሲ.ደብልዩ ሀሪስ | | |
| ጂሲ ኔይሊ አንደኛ ደረጃ | | |
| ኪምባል አንደኛ ደረጃ | | |
| ፐሉመር አንደኛ ደረጃ | | |
| **ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 8)** | | |
| ሂንድሊይ አንደኛ ደረጃ | ሀርት መከከለኛ ትምህርት ቤት | ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ኪንግ አንደኛ ደረጃ | | |
| ሌክይ አንደኛ ደረጃ | | |
| ፓአተርሰን አንደኛ ደረጃ | | |
| ሲሞን አንደኛ ደረጃ | | |
| ጋርፊልድ አንደኛ ደረጃ | ጆንሰን መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ማልኮም ኤክስ አንደኛ ደረጃ | | |
| ተርነር አንደኛ ደረጃ | | |
| **ካርዶዛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 1)** | | |
| ኤች ዲ. ኩክ አንደኛ ደረጃ | ኮሎምቢያ ሀይትስ መካከለኛ ትምህርት ቤት | ካርዶዛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ተብማን አንደኛ ደረጃ | | |
| ክሊቭላንድ አንደኛ ደረጃ | ኒው ሴንተር ሲቲ መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ጋሪሰን አንደኛ ደረጃ | | |
| መሪ ሪድ አንደኛ ደረጃ | | |
| ሮስ አንደኛ ደረጃ | | |
| ሲተን አንደኛ ደረጃ | | |
| ቶምሰን አንደኛ ደረጃ | | |
| ኤስደብልዩ ደብልዩ በ ፍራሲስ-ስቲቨንስ EC | | |

| | | |
|---|---|---|
| **ኩሊጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 4)** | | |
| ብራይትወድ አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲለወጥ የታቀደ) | ኒው ኖርዝ መካከለኛ ትምህርት ቤት | ኩሊጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ላሳሌ--ባከስ አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ታኮማ አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ዊትየር አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| **ደንባር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 5)** | | |
| ባንከር ሂል አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) | ብሩክላንድ መካከለኛ ትምህርት ቤት | ደንባር ሁለተኛ ደረጃ |
| ቦሮውስ አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ላንግዶን አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ኖይስ አንደኛ ደረጃ ((ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ላንሊ አንደኛ ደረጃ | ማክንሊ ቴክ ኢዲ ካምፓስ (6-8) | |
| ዊሂትሊ አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ዋከር-ጆንስ EC | | |
| **ኢስተርን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 6)** | | |
| ብራውኒ PS-8 | | ኢስተርን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ካፒቶል ሂል ሞንትሶሪ @ሎገን PS-8 (ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት ካለወሰን) | | |
| ሞውሪይ አንደኛ ደረጃ | ኢሎት-ሀይን መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ማይነር አንደኛ ደረጃ | | |
| ፔይን አንደኛ ደረጃ | | |
| ትምህርት ቤት- በትምህርት ቤት ውስጥ (ከተማ አቀፍ ትምህርት ቤት ካለ አዋሳኝ) | | |
| አሚዶን-ቦውንስ አንደኛ ደረጃ | ጀፈርሰን አካድ መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ብሬንት አንደኛ ደረጃ | | |
| ታይለር አንደኛ ደረጃ | | |
| ቫን ነስ አንደኛ ደረጃ | | |
| ጄ.ኦ. ዊልሰን አንደኛ ደረጃ | ስቱዋርት-ሆብሰን መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ሉድሎው-ቴይለር አንደኛ ደረጃ | | |
| ፒቦዲይ/ዋትኪንስ አንደኛ ደረጃ | | |

| | | |
|---|---|---|
| **ሩዘቨልት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 4)** | | |
| ባርናርድ አንደኛ ደረጃ | ማክፋርላንድ መካከለኛ ትምህርት ቤት | ሩዘቨልት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ብሩስ-ሞንሮ አንደኛ ደረጃ | | |
| ፓዎል አንደኛ ደረጃ | | |
| ሬይመንድ አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ትሩሰዴል አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| ዌስት አንደኛ ደረጃ (ወደ አንደኛ ደረጃ እንዲለወጥ የታቀደ) | | |
| **ዊልሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 3)** | | |
| ባንክሮፍት አንደኛ ደረጃ | ዲል መካከለኛ ትምህርት ቤት | ዊልሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ኸርስት አንደኛ ደረጃ | | |
| ጄኒይ አንደኛ ደረጃ | | |
| ላፍያት አንደኛ ደረጃ | | |
| ሙርች አንደኛ ደረጃ | | |
| ሼፐርድ አንደኛ ደረጃ | | |
| ኢቶን አንደኛ ደረጃ | ሀርዲይ መካከለኛ ትምህርት ቤት | |
| ሀይድ/አዲሰን አንደኛ ደረጃ | | |
| ኪይ አንደኛ ደረጃ | | |
| ማን አንደኛ ደረጃ | | |
| ስቶደርት አንደኛ ደረጃ | | |
| አይስተር-አዳምስ EC | | |
| **ውድሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዋርድ 7)** | | |
| ኤይቶን አንደኛ ደረጃ | ኬልይ ሚልስ መካከለኛ ትምህርት ቤት | ውድሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| በርቪል አንደኛ ደረጃ | | |
| ድሪው አንደኛ ደረጃ | | |
| ሂውስተን አንደኛ ደረጃ | | |
| ስሞዘርስ አንደኛ ደረጃ | | |
| ቶማስ አንደኛ ደረጃ | | |
| | ሮን ብራውን የተመረጠ/የተለየ መካከለኛ ትምህርት ቤት | |

# የታቀደው የፕሮግራም ዝውውር መንገዶች ዕቅዶች

<table>
<tr><th colspan="3">ባለ ሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች</th></tr>
<tr><td>የለም</td><td>CHEC መካከለኛ ትምህርት ቤት</td><td rowspan="3">ኑዘሸልት DL ፕሮግራም</td></tr>
<tr><td colspan="2">አይስተር-አዳምስ ቢሊጉዋል EC</td></tr>
<tr><td>ባንክሮፍት አንደኛ ደረጃ<br>ብሩስ-ሞንሮ አንደኛ ደረጃ<br>ክሊቭላንድ አንደኛ ደረጃ DL ፕሮግራም<br>መሪ ሪድ አንደኛ ደረጃ ፕሮግራም<br>ፓዎል| አንደኛ ደረጃ DL ፕሮግራም<br>ታይለር DL ፕሮግራም</td><td>ማክፋርላንድ DL ፕሮግራም</td></tr>
</table>

<table>
<tr><th colspan="3">ስቴም ፕሮግራሞች</th></tr>
<tr><td>የለም</td><td>ማክንሊ መካከለኛ ትምህርት ቤት</td><td>ውድሰን ሁለተኛ ደረጃ</td></tr>
</table>

# የአማካሪ ኮሜቴ ዓባሎች

| | |
|---|---|
| **አቢጌል ስሚዝ፣** የትምህርት ምክትል ከንቲባ፣ ሊቀመንበር | |
| **የማህበረሰብ ተወካዮች** | |
| **ማርያም አህራንጅ፣** ዋርድ 1፣ ወላጅ<br>ማርሻል ብሬናን ኮንስቲትዩሽናል ሊትራሲ ፕሮጀክት፣ አሜሪካን ዩኒቨርስቲ | **ኤምሊይ ብሉምፊልድ፣** ዋርድ 2፣ ኗሪ<br>የቅድሞ ዓባል፣ ዲ.ሲ. የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ፣ የቻርተር ኦፕሬተር |
| **ዊልማ ቦነር፣** ዋርድ 4፣ ኗሪ<br>ሀዋርድ ዩኒቨርስቲ | **ኤድ ዴቪስ፣** ዋርድ 4, ኗሪ<br>ችልድረን ዩዝ ኢንቬስመንት ትራስት ኮርፖሬሽን |
| **ዴኒስ ፎርት፣** ዋትድ 6, DCPS ወላጅ | **ማቲው ፍሩሚን፣** ዋርድ 3፣ DCPS ወላጅ<br>ANC- 3E ኮሚሽነር |
| **ሄዘር ሀርዲንግ፣** ዋርድ 5፣ የPCS ወላጅ<br>ዘ ኢድ ኮሶርትየም ፎር ሪሰርች እና ግምገማ (EdCORE) | **ፌይዝ ሀባርድ፣** ዋርድ 5፣ ኗሪ፣ ወላጅ<br>ዋርድ 5 የትምህርት ካውንስል፣ ዲ.ሲ. የላይብራሪ ባለ አደራዎች |
| **ረቨረንድ ዶናል አይሳቅ፣** ዋርድ 7፣ ኗሪ<br>ኢስት ኦፍ ዘ ሪቨር ክለርጂ፣ ፖሊስ፣ ማህበረሰብ ህብረት፣ ኢንተር ፌይዝ ካውንስል | **ካሚል ኪሮስ፣** ዋርድ 8፣ PCS ወላጅ<br>አችቨመንት ፕሬፕ ቦርድ ኦፍ ትራስቲስ |
| **ካቲይ ሬሊይ,** ዋርድ 4 ፣ ኗሪ<br>ሲንየር ሀይ አሊያንስ ኦፍ ፓሬንትስ ፕሪንሲፓልስ እና ኤዱኬተርስ (SHAPPE)፣ ዋርድ 4 ኤዱኬሽን አሊያንስ | **ሻረን ሮቢንሰን፣** ዋርድ 8, DCPS ወላጅ<br>ዋርድ 8 ኤዱኬሽን ካውንስል፣ ባሉ ሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት የወላጆች ኮሚቴ |
| **ኤቨሊን ቦይድ ሲሞንስ፣** ዋርድ 2፣ DCPS ወላጅ<br>ANC-2F የትምህርት ኮሚቴ ተባባሪ ሊቀ መንበር<br>ዋርድ 2 ኢዲ ኔትዎርክ | **ኢቦኒ-ሮዝ ቶምፕሰን፣** ዋርድ 7፣ ኗሪ<br>ሴቭ ዘ ችልድረን ዩኤስ፣ ዋርድ 7 ኤዱኬሽን ካውንስል፣ ላስት ፎር ፕሉመር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| **ማርታ ዩርክዊላ፣** ዋርድ 4፣ PCS ወላጅ | **ማርትን ዌልስ፣** ዋርድ 6፣ DCPS ወላጅ<br>ፌደራል የሥራ እና የመቅጠር ጠበቃ፣ አሚዶን-ቦውን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የወላጆች ኮሚቴ |
| **የዲስትሪክት ኤጀንሲ ተወካዮች** | |
| **ጆሴፊን ባያስ-ሮቢንሰን፣** የቤተሰብ እና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ ዲ.ሲ. የሕዝብ ትምህርት ቤቶች | **ክላራ ሄስ፣** ዲሬክተር፣ ሂዩማን ካፒታል እና ስትራተጂክ ኢንሽየቲቭስ፣ ዲስ. የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቦርድ |
| **ክሪስቶፈር ዴልፍስ፣** ከተማ አቀፍ ፕላን አውጭ፣ ዲ.ሲ. ፕላኒግ ቢሮ | **ኤለን ማካርቲይ፣** ጊዜያዊ ዲሬክተር፣ ዲ.ሲ. ፕላኒግ ቢሮ |
| **አርያና ኪዊኖእስ፣** የሠራተኞች የበላይ አለቃ፣ የምክትል ከንቲባው የጤና እና የህዝብ አገልግሎቶች | **ኢሪስ ቦንድ ጊል፣** የግራንት አያያዝ እና ማስከበር፣ ዲሲ የትምህርት ተቆጣጣሪ ቢሮ |


DC ACHIEVERS SEMI-FINALISTS

## Tell us what you think!

**Complete a feedback form by July 21st at dme.dc.gov/boundaries**

**Email your concerns and questions to dme.studentassignment@dc.gov or call 202-478-5738**